

# ኢየሱስና ሐዋሪያቱ

ኢየሱስ የሚረዱት ልዩ ተከታዮችን ይፈልግ ነበር።እነኝህም ሐዋርያት ተብለው ይጠራሉ።

የመጀመሪያወቹ ሐዋርያት አሳ አጥማጆች የነበሩት ስምኦን ጴጥሮስና ወንድሙ እንድርያስ ነበሩ። እንደዚሁም ሌሎች በዓሳ ማጥመድ ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ሁለት ደቀ መዛሙርት ጠራ። እነርሱም የዘብዴዎች ልጆች የሚባሉት ያዕቆብና ዮሐንስ ናቸው።

በኋላም ፊሊጶስን፣ በርጠሎሜዎስንና(ናትናኤልን) ማቴዎስን ጠራቸው።. በተጨማሪም ሌሎች አምስት ለሐዋርያነት የተመረጡ ነበሩ።

እነኝህን የኢየሱስ ተከታዮችን ለማስታወስ የሚረዳን መዝሙር እንማራለን።

ኢየሱስ አንድ በአንድ ጠራቸው
ጴጥሮስ፣ እንድርያስና ዮሐንስ
በመቀጠልም ፊሊጶስና ቶማስ
እንዲሁም ማቴዎስና በርጠሎሜዎስ
ታናሽ ብለው የሚጠሩትን ያዕቆብንም
ስምኦንንና ታዲዮስንም
የመጨረሻው ተጠሪም ይሁዳ
ኢየሱስን ለመሸጥ የከዳ፣

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሳና ወደአባቱ ከሄደ በኋላ ኢየሱስን ለሞት አሳልፎ በሰጠው በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ ማቲያስ የኢየሱስ ሐዋርያ እንዲሆን ተመረጠ።

በኋላም ጳውሎስ ሐዋርያ እንዲሆን ተመረጠ።  አብዛኛዎቹን የአዲስ ኪዳን መልእክቶች የፃፈውም እርሱ ነው።

*ይህ ታሪክ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 1፡ 35 – 49 እና በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 1፡ 12 – 26 ባለው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ይገኛል።*

http://gardenofpraise.com